# የደቀ መዝሙርነት መርሖዎች

## የትምህርቱ መስረታዊ ሃሳቦች

### የወንጌል ሥርጭት መንደርደሪያ

### ትምሕርት 1፥ ዓለምን በወንጌል የመድረስ ጥሪ

የአንድ አማኝ ክርስቲያን ዓላማ፣ በሕይወቱም ሆነ በአገልግሎቱ ዉስጥ፡- የእግዚአብሔርን ዓላማ ፈልጎ ሊደርስበትና በሚገባ አዉቆት፤ ከእርሱም ጋራ ኅብረት በማድረግ በክንዋኔዉ ላይ አብሮ መሳተፍ ነዉ። ይህ ትምሕርት፥ እግዚአብሔር ለሕይወትህ ያለዉን ዓላማ ለመፈፀም ከእርሱ ጋር ተስማምተህ ስትተጋ፤ የራስህን እይታ ከእግዚአብሔር ፈቃድና እይታ ጋር በማጣጣም እንድትራመድ ይረዳሃል።

እግዚአብሔር ለሕይወትህ ያለዉን ዓላማ እስከ ገለጠልህ ድረስ፣ በሚገባ አከናዉነህ ከፍፃሜዉ እንድታደርስ ይጠብቅብሃል። በንባቡ ስትገፋበት፡- እግዚአብሔር አንተ በፊቱ እንድትሄድ በሚፈልግባቸዉ መንገዶች ሁሉ፣ እንዴት ወደፊት መራመድ እንደምትጀምር ግንዛቤ ትጨብጣለህ።

## ልብ በል

የእግዚአብሔር ዓላማ ነፍሳትን ማዳን ነዉ፤ ለዚህም ነዉና ልጁን ወደ ዓለም የላከዉ። ኢየሱስ ክርስቶስም የእግዚአብሔርን ዓላማ በትክክል ተረዳ፤ አባቱንም በሚያስደስትና በሚያረካ ሁኔታ ምላሽን ሰጠ። ልክ እንደ ኢየሱስ ክርስቶስ፣ እኛም ወጥተን የጠፉትን ፈልገን፥ እረኛ እንድንሆናቸዉ እግዚአብሔር ይፈልጋል። ለሕይወታችን ያለዉ እቅድና ዓላማ ይኸዉ ነዉና።

ኢየሱስ መለኮታዊ ሥልጣንና ክብሩን፣ እንዲሁም ከአምላክነቱ ጋራ የሚጎዳኙ ወይም የሚዛመዱ መብቶቹን ሙሉ በሙሉ ትቶ፤ እድለኛ ያልነበሩትን ምስኪን በጎች ለመንከባከብ እራሱን ሰጠ። ዛሬ ጌታችን ኢየሱስ፥ አንተም በተራህ ያንኑ እንድታደርግ ይጠራሃል፦ ‘ተደላድለህ ከአለህበት ከምቾት ቀጠናህ ዉጣ፤ በእግዚአብሔርም የእርሻ መከር ላይ ሠራተኛ ሁን!’

በሕይወት ዉስጥ ዓላማዬ ምንድን ነዉ? በዚህስ ዘመን፥ በዚህ ሥፍራ ያለሁት ለምንድን ነዉ? ያ ምናልባትም የሰብአዊ ፍጡር ኀልዉና ወይም የመኖር ጥያቄ ስለሆነ፤ ለፈላስፋዎች መተዉ መልካም ነዉ የሚሉ ጥቂቶች አይደሉም። ነገር ግን፥ በአንድም ሆነ በሌላ ጊዜ፤ ማንኛዉንም ሰዉ የሚያስጨንቅና የሚያነጋግር ጥያቄ መሆኑ ተረጋግጧል። አንዳንዶች መልስ ለማግኘት ያልሞከሩት ነገር የለም፦ የተለያዩ እምነቶችን፣ የእምነት መሪዎችን እና፣ ጠበብቶችን፣ እራስን በራስ ማሻሻያ መርሐ-ግብሮችን፣ ወይንም ደግሞ፥ ከሁሉ የላቀ አንድ ነገር ላይ መድረስን፣ ይኸዉም ለሕይወታቸዉ ትርጉም የሚሰጣቸዉን፤ እንዲሁም የጠራ አቅጣጫ የሚያስይዛቸዉን ዓላማ ለመጨበጥ መሞከር ነዉ። በሕይወታቸዉ ዉስጥ የሚኖረዉን ዓላማ ፈልገው ለማግኘት በሚያደርጓቸዉ ሙከራዎች፤ የገዛ ሕይወታቸዉን ያጠፉ፤ ወይም በተፈጥሮ ከተለመደዉ አሟሟት ዉጭ፣ በለጋ እድሜአቸዉ የተቀጩ እጅግ ብዙ ወጣቶች ናቸዉ። እንዲያዉም ከእነዚህ ሰዎች አብዛኞቹ፦ ኃብታሞች፥ ታላቅ ተሰጥኦ ያላቸዉና ዝነኞች ናቸዉ፤ ነገር ግን በሆነ ምክንያት፣ ደስታ ሸሽቶ ይርቃቸዋል። ይህ የተለየና የማይገባ እንግዳ ነገር ነዉ፤ አይደለም እንዴ? አብዛኞቻችን እንደምናምነዉ፥ በዚህ ምድር ላይ ያለን ዓላማ፦ ብዙ ገንዘብን በማግኘት፤ የተመቻቸና የተደላደለ ሕይወትን መምራት ነዉ። በመሠረቱ፥ እሴታችንን የምንመዝነዉ፦ በንክ ዉስጥ በአጠራቀምነዉ ገንዘብ ብዛት፣ ወይም ደግሞ፥ በተሸከምነዉ ሥልጣን ኃይል፤ እንዲሁም በአካበትነዉ ኃብትና ንብረት ነዉ።

በዛሬዉ ዘመን፥ ለስኬታማነት ያለዉ ምኞትና ጉጉት፣ የወጣቱ ትዉልድ ባሕርይ ወይም መለያ ተደርጎ የተወሰደ ይመስላል። ነገር ግን፥ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በምድር ላይ በነበረበትም ጊዜ እንኳን፣ ነገሮች ብዙም ከዚህ የተለዩ አልነበሩም። ሉቃስ 12:15-21 ላይ፥ ጌታ ኢየሱስ፥ አብዛኞቻችን ከራሳችን ጋራ ልናዛምድ የምንችለዉን ታሪክ ይነግረናል፦ “የሰው ሕይወት በገንዘቡ ብዛት አይደለምና ተጠንቀቁ፥ ከመጐምጀትም ሁሉ ተጠበቁ አላቸው።‘ምሳሌም ነገራቸው እንዲህ ሲል፦ አንድ ባለ ጠጋ ሰው እርሻ እጅግ ፍሬያም ሆነችለት። እርሱም፦ ፍሬዬን የማከማችበት ስፍራ አጥቻለሁና ምን ላድርግ? ብሎ በልቡ አሰበ። እንዲህ አደርጋለሁ፤ ጐተራዬን አፍርሼ ሌላ የሚበልጥ እሠራለሁ፥ በዚያም ፍሬዬንና በረከቴን ሁሉ አከማቻለሁ፤ ነፍሴንም፦ አንቺ ነፍሴ፥ ለብዙ ዘመን የሚቀር ብዙ በረከት አለሽ፤ ዕረፊ፥ ብዪ፥ ጠጪ፥ ደስ ይበልሽ እላታለሁ አለ። እግዚአብሔር ግን፦ አንተ ሰነፍ፥ በዚች ሌሊት ነፍስህን ከአንተ ሊወስዱአት ይፈልጓታል፤ ይህስ የሰበሰብኸው ለማን ይሆናል? አለው። ለራሱ ገንዘብ የሚያከማች፥ በእግዚአብሔር ዘንድም ባለ ጠጋ ያልሆነ እንዲህ ነው።” ይህ ታሪክ የሰዉ ልጅ በሕይወቱ ያለዉ ዓላማ፤ ከእግዚአብሔር ዓላማ ጋራ ያለዉን ተቃርኖ በሚገባ ፈትቶ ያስረዳል። ምናልባትም የዓለም መልክ ነዉና፣ ሰዎች ይህንን ኃብታም ገበሬ፥ በኃብቱና በሥልጣኑ ምክንያት ያከብሩት፤ አልፈዉም ሊቀኑበት ይችላሉ። እግዚአብሔርን ግን የሚያሳስበዉ፥ የምትጠፋዉ የገበሬዉ ነፍስ ናት። የእግዚአብሔር ዓላማ ነፍሳትን ማዳን ነዉ፤ ለዚህም ነዉና ልጁን ወደ ዓለም የላከዉ። ኢየሱስ ክርስቶስም የእግዚአብሔርን ዓላማ በትክክል ተረዳ፤ አባቱንም በሚያስደስትና በሚያረካ ሁኔታ

ምላሽን ሰጠ።

ልክ እንደ ኢየሱስ ክርስቶስ፣ እኛም ወጥተን የጠፉትን ፈልገን፥ እረኛ እንድንሆናቸዉ እግዚአብሔር ይፈልጋል። ለሕይወታችን ያለዉ እቅድና ዓላማ ይኸዉ ነዉና። ማቴዎስ 9:35-38 ላይ እንዲህ እናነባለን:- 'ኢየሱስም በምኩራቦቻቸው እያስተማረ፥ የመንግሥትንም ወንጌል እየሰበከ፥ በሕዝብም ያለውን ደዌና ሕማም ሁሉ እየፈወሰ፥ በከተማዎችና በመንደሮች ሁሉ ይዞር ነበር። ብዙ ሕዝብም ባየ ጊዜ፥ እረኛ እንደሌላቸው በጎች ተጨንቀው ተጥለውም ነበርና አዘነላቸው። በዚያን ጊዜ ደቀ መዛሙርቱን:- መከሩስ ብዙ ነው፥ ሠራተኞች ግን ጥቂቶች ናቸው፤ እንግዲህ የመከሩን ጌታ ወደ መከሩ ሠራተኞች እንዲልክ ለምኑት አላቸው።"

ጌታ ኢየሱስ፥ ለጠፉት የእግዚአብሔር ልጆች የአለዉ ከፍተኛ ርኅራኄ ስለሚያበረታታዉ ነዉ፤ ወደ እነርሱ ሄዶና ፈልጎ፤ እረኛ የሆናቸዉና ያሰማራቸዉ። ብዙዎቹ ዛሬም እንደሚሆኑት:- አቅጣጫ ያልነበራቸዉ፥ የተጎዱ፥ ጠፍተዉ የባከኑ፥ እና ብቸኞች ነበሩ። ኢየሱስ መለኮታዊ ሥልጣንና ክብሩን፣ እንዲሁም ከአምላክነቱ ጋራ የሚጎዳኙ ወይም የሚዛመዱ መብቶቹን ሙሉ በሙሉ ትቶ፤ እድለኛ ያልነበሩትን ምስኪን በጎች ለመንከባከብ እራሱን ሰጠ። ዛሬ ጌታችን፥ አንተም በተራህ ያንኑ እንድታደርግ ይጠራሃል:- 'ተደላድለህ ከአለህበት ከምቾት ቀጠናህ ዉጣ፤ በእግዚአብሔርም የእርሻ መከር ላይ ሠራተኛ ሁን!' እንደ እዉነቱ ከሆነ ዛሬም፥ እጅግ የባሰ የሠራተኞች እጥረት አለ። እንግዲህ ታጥቀህ ተነስተህ በእግዚአብሔር ሥራ ላይ በመሳተፍ፣ የሠራተኞችን ቁጥር ማሳደግ ትችላለህ። በሌላ በኩል ደግሞ፥ ከእረኛህ ከክርስቶስ ጋር እንኳን በመተባበር ስትሠራ፤ ተጨማሪ ሠራተኞች እንዲላኩና እንዲበዙ መፀለይን አትዘንጋ። በተጨማሪም፥ የምትሰብከዉን መኖርህን አስታዉስ በየዕለቱም ትጋ። 1ኛ ቆሮንቶስ 10:31 ላይ ጳዉሎስ በትክክል እንዲህ ይላል:- "እንግዲህ የምትበሉ ወይም የምትጠጡ ብትሆኑ ወይም ማናቸውንም ነገር ብታደርጉ ሁሉን ለእግዚአብሔር ክብር አድርጉት።" እንደ አማኝ ክርስቲያን፥ ዓለማዊዉ ወይም መንፈሳዊ ያልሆነዉ የዚህ ምድር ዕለት ከዕለት ኑሮህ፤ ከክርስትናዉ ጥሪህ የተገለለ እንደሆነ በማሰብ፣ ሕይወትህን ልትከፋፍለዉ አትችልም። የሕይወትህ ዓላማ የእግዚአብሔርን ክብር ማወጅ፤ ሉአላዊነቱና መልኩ፣ በአንደበትህና በድርጊቶችህ፣ በሁለንተናዊ ሕይወትህ ሁሉ ጎልቶ እንዲታይ ማድረግ ነዉ።

## በጥልቀት እንይ

1ኛ ቆሮንቶስ 10:31 ላይ ጳዉሎስ በትክክል እንዲህ ይላል:- "እንግዲህ የምትበሉ ወይም የምትጠጡ ብትሆኑ ወይም ማናቸውንም ነገር ብታደርጉ ሁሉን ለእግዚአብሔር ክብር አድርጉት።" እንደ አማኝ ክርስቲያን፥ ዓለማዊዉ ወይም መንፈሳዊ ያልሆነዉ የዚህ ምድር ዕለት ከዕለት ኑሮ፤ ከክርስትናዉ ጥሪህ የተገለለ እንደሆነ በማሰብ፣ ሕይወትህን ልትከፋፍለዉ አትችልም። የሕይወትህ ዓላማ የእግዚአብሔርን ክብር ማወጅ፤ ሉአላዊነቱና መልኩ፣ በአንደበትህና በድርጊቶችህ፣ በሁለንተናዊ ሕይወትህ ሁሉ ጎልቶ እንዲታይ ማድረግ ነዉ።

በጌታ ኢየሱስ እንድንፈፅመዉ የተሰጠን ተልእኮ፥ ሁለት እጥፍ በመሆኑ፥ ወንጌልን በመስበክ ብቻ በቀላሉ የሚያበቃ ተግባር አይደለም። ማቴዎስ 28:19-20 ዉስጥ ጌታ ኢየሱስ በግልፅ እንዲህ ይናገራል:- "እንግዲህ ሂዱና አሕዛብን ሁሉ በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው፥ ያዘዝኋችሁንም ሁሉ እንዲጠብቁ እያስተማራችኋቸው ደቀ መዛሙርት አድርጓቸው፤ እነሆም እኔ እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ሁልጊዜ ከእናንተ ጋር ነኝ።" በመሠረቱ ደቀ መዝሙርነት፥ የታላቁ ተልእኮ ወሳኝ እና ዓይነተኛ አካል ነዉ። በሌላ አባባል፥ ከሁሉ አስቀድመህ የጌታ ኢየሱስ ደቀ መዝሙር መሆን ይጠበቅብሃል፤ ከዚያም እርሱን በመከተልና

በመማር፣ መንገዱን ታዉቃለህ፣ ከራስህም አልፈህ ለሌሎች ትክክለኛዉን መንገድ ታሳያቸዋለህ ትመራቸዉማለህ። የደቀ መዝሙርነት ሂደት፡-በእግዚአብሔር መንፈስ ዉስጥ ማደግንና፣ ይበልጥ ክርስቶስን ወደ መምሰል መድረስን ያካትታል። ዕብራዉያን 5:12-14 በአካላዊ እና በመንፈሳዊው እድገት መካከል፣ ታላቅ ተምሳሌያዊ ነፅፅርን ያቀርባል፡- 'ከጊዜው የተነሳ አስተማሪዎች ልትሆኑ ሲገባችሁ፥ አንድ ሰው ስለ እግዚአብሔር ቃላት መጀመሪያ ያለውን የሕፃንነትን ትምህርት እንዲያስተምራችሁ እንደ ገና ያስፈልጋችኋልና፤ የሚያስፈልጋችሁም ወተት ነው እንጂ ጠንካራ ምግብ አይደለም። ወተት የሚጋት ሁሉ ሕፃን ስለ ሆነ የጽድቅን ቃል አያውቅምና፤ ጠንካራ ምግብ ግን መልካሙንና ክፉውን ለመለየት በስራቸው የለመደ ልቡና ላላቸው ለፍጹማን ሰዎች ነው።' ደቀ መዝሙርነት ከእምነታችን መሠረታዊ ትምሕርት የሚጀምር ቢሆንም፣ የእግዚአብሔርን ቃል ፥ መጽሐፍ ቅዱስን በጥልቀት ማጥናትና መመርመር ደግሞ፣ የአማኙን ክርስቲያናዊ ማንነትና ብቃት ለመገንባት ይረዳል። ሌሎች ደቀ መዛሙርትን የሚያፈራ ብቁ ደቀ መዝሙር ወይም አገልጋይ ስትሆን፤ ልክ ጌታ ኢየሱስ፡- 'ያዘዝኋችሁንም ሁሉ እንዲጠብቁ እያስተማራችኋቸው..' ብሎ እንደ አዘዘህና ተልእኮዉን እንደ አስረከበህ፤ አንተም ተከታይ ተማሪዎችህ፥ መጽሐፍ ቅዱስን በሙላት እንዲያነብቡ ማበረታታት ይጠበቅብሃል።

ምንም እንኳን የወንጌል ሥርጭት፥ አንዳንድ ጊዜ ተስፋ አስቆራጭ ቢመስልም፤ የምሥራቹን ቃል ለመመስከር ስትዘረጋ፣ እግዚአብሔር ለሕይወትህ ያለዉን ዓላማ እያሟላህ የመሆኑን እዉነት ማወቅህ ነዉና፤ አገልግሎትህንም ደስ የሚያሰኝ ልምምድ ያደርገዋል። በመሠረቱ፥ እግዚአብሔር ለሕይወታችን ያለዉን እቅድና ዓላማ ባይገልጥልን ኖሮ፤ እንዲያዉ ዓላማ ቢስ ሆነን፣ እረኛ እንደሌላቸዉ በጎች ጠፍተን በተቅበዘበዝን ነበርን። ዛሬ እኛም፡- ከእግዚአብሔር ጋራ አካልና አጋሩ ሆነን፥ ከእርሱ ጋራ ኅብረትን በማድረግ፣ ብዙ በጎችን ወደ በረቱ ለማስገባት፤ ወደ መንጋዉ፥ ወደ ሰፊዉም ቤተሰቡ ነፍሳትን ለመጨመር፤ ቃል መግባትና ማረጋገጥ ይኖርብናል።

## ማጠቃለያ

•አብዛኞቻችን እንደምናስበዉ፤ የሕይወታችን ዓላማ፡- ዳጎስ ያለ የባንክ ተቀማጭ ኖሮን፣ የተመቻቸ ጣፋጭ ሕይወትን መምራት መቻል ነዉ። ይሁን እንጂ፥ ሉቃስ 12:16-20 ላይ የተመለከትነዉ የኃብታሙ ገበሬ ታሪክ እንደሚያሳየን፤ እግዚአብሔርን የሚያሳስበዉ 'የነፍሳችን ጤንነት' መሆኑን ነዉ።

• እግዚአብሔር ለዓለም ያለዉ እቅድ ነፍሳትን ማደን ነዉ፤ ለዚህም ነዉ፥ ለኃጢአታችን በሞቱ ዋጋ እንዲከፍልልን ልጁን የላከልን። የእግዚአብሔርን ዓላማ እንደ ተገነዘበዉ፣ ልክ እንደ ኢየሱስ ክርስቶስ፣ የጠፉትን ነፍሳት ፈልገን እረኛ ልንሆናቸዉ እንድንችል፤ እይታችንን ከእግዚአብሔር አተያይ ጋራ ማስማማትና ማጣጣም ይገባናል። ያ ነዉ እግዚአብሔር ለሕይወታችን ያለዉ ዓላማ!

•አንድ አማኝ ክርስቲያን፥ በየዕለቱ የሚኖርበትን የምድራዊ ሕይወቱን፤ ከመንፈሳዊ ጥሪዉና አገልግሎቱ መለየት ወይም ከፋፍሎ ማየት አይችልም። በሚያደርጋቸዉ በማናቸዉም ነገሮች ሁሉ ለእግዚአብሔር ክብርን መስጠት ይገባዋል (1ኛ ቆሮንቶስ 10:31)።

- ጌታ ኢየሱስ በታላቁ ተልእኮ (ማቴዎስ 28:16-20) ዉስጥ፤ በሰጣቸዉ ሁለት መመሪያዎች መሠረት፥ እንደ እግዚአብሔር አምባሳደሮች:- የወንጌልን የምሥራች ቃል እንድንሰብክ፤ ደቀ መዛሙርት እንድናፈራና እንድናበዛ ተጠርተናል።

- ደቀ መዝሙርነት:- ከአዲስ አማኝነት፥ እግዚአብሔር ቃል ዉስጥ ጠልቆ ወደ ተተከለ ሰዉ የመሸጋገር፤ ብሎም ክርስቶስን የበለጠ ለመምሰል ወደ በሰለ ብቁ አገልጋይነት፤ የማደግ ሂደት ነዉ። እንደ ወንጌላዉያን፥ አዲስ አማኝ ክርስቲያኖች፥ የእግዚአብሔርን ቃል ሳያሰልሱ እንዲመገቡ ማበረታታት የራሳችሁ ኃላፊነት መሆኑን ልብ በሉ (ዕብራዉያን 5:12-14)።

## እርስዎስ ምን ይላሉ?

- እግዚአብሔር ለአንተ ሕይወት ያለዉ ዓላማ፣ ከአንተ ዓላማ ጋራ የሚጣጣመዉ እንዴት ነዉ? ሁለቱን ዓላማዎች ለማቀናጀትስ ምን ማድረግ ትችላለህ?

- ስለ ወንጌል ሥርጭት እና የጠፉትን ስለ መድረስ፣ ያለህ ግላዊ አመለካከት ምን ይመስላል?

- ለሌሎች ሰዎች በመመስከር ተልእኮ ወቅት፣ የሚያጋጥሙህን ተግዳሮቶች የምትወጣዉ እንዴት ነዉ?

- አዲስ አማኝ ክርስቲያኖችን፥ ብቁ እና ዉጤታማ ደቀ መዛሙርት ለማድረግ፣ የምትጠቀመዉ ስልት ምንድን ነዉ? አቀራረብህስ ምን ይመስላል?

- ከእግዚአብሔር ጋራ በትክክል ለመራመድ የሚያበቃህ እድገት ላይ ለመድረስ ምን ማድረግ ትችላለህ?

ሁሉም የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች በ1954 ዓም ከታተመዉ የድሮዉ (KJV) ትርጉም ሲሆን፥ በኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማህበር ፈቃድ ተቀድተዉ የታተሙ ናቸዉ።

ሌሎች ሁሉም ይዘቶች የ © 2019 ትራንስ ዎርልድ ራዲዮ ካናዳ ነው። ይህንን ግብአት ለመጠቀም ዋጋ እስካልጠየቁ ድረስ እና ስለ ክርስቶስ አለምን መድረስን አላማዎ አድርገዉ እስከሰሩ ድረስ በፈለጉት አይነት መንገድ ሊጠቀሙበት ይችላሉ። ተጨማሪ የፍቃድ ዝርዝሮችን በ www.discipleshipessentials.org/licensing ይመልከቱ.